**የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን)** **National Movement of Amhara (NAMA)**

# ከአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) የተሰጠ መግለጫ

የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) በትህነግ መራሹ የትግራይ ክልላዊ መንግስት በኃይል ወደ ትግራይ በተካለሉ አካባቢዎች እየወሰደ ያለውን ኢሰብአዊ ድርጊት በጽኑ ያወግዛል። አብን ዜጎች የማንነት ጥያቄ በማንሳታቸው ብቻ እየተወነጀሉ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ተይዘው ለእስርና እንግልት ሊዳረጉ እንደማይገባ አጥብቆ ያምናል። የማንነት ጥያቄ ተፈጥሯዊና በአስተዳደር አካላት ይሁንታ ሊሰጥም ሆነ ሊነፈግ የማይገባው በመሆኑ ጥያቄ ያቀረበውን ሕዝብ በመድመጥ ይኸው መብት በአግባቡ ምላሽ ሊሰጠው እንደሚገባም አብን ይረዳል።

ከዚህ በተፃራሪው ትህነግ መራሹ የትግራይ ክልል መንግስት ያለሕዝብ ይሁንታና መልካም ፈቃድ በፖለቲካ ውሳኔና ኃይል ጭምር የወልቃይት፣ጠለምት፣ጠገዴና ራያ አማራ ሕዝብና መሬቶች ከአማራ ተቆርሰው ወደ ትግራይ ክልል መካተታቸውን ተከትሎ ውሳኔውን የተቃወሙ ወገኖች እንደወንጀለኛ ተቆጥረው ከሩብ ክፍለዘመን በላይ ለዘለቀ አስከፊ ኢሰብአዊ ድርጊቶች ተጠቂ ሆነዋል።

ይኸው የጭቆናና አምባገናዊነት ሥርዓትና ሥሪት ዛሬም ድረስ ቀጥሎ ከታች በምስሉ እንደሚታየው የትግራይ ክልል መንግስት አማራ ነኝ ባሉ የጠገዴ አማራዎች ላይ ጭካኔ በተሞላበት አኳኋን እስርና አፈና እያካሄደ ነው። መሰል ኢሰብአዊ ድርጊቶች ለአማራነታችን ያለንን ታማኝነትና ፅናት የሚጭምር እንጂ አንዲት ጋት እንኳን ወደኋላ የሚመልስ አይሆንም። አማራነት ስጋት የማይሆንበትን ሥርዓትና ሥሪት አቁመን ሕዝባችንን ባለአገርና ባለመንግስት እስክናደርግ ድረስ ትግላችንን አጠናክረን የምንቀጥል ይሆናል። የትግራይ ክልል መንግስት በአማራ ላይ እያደረሰ ያለው ኢሰብአዊ ድርጊት ነውረኝነት የተሞላበት ፀረ አማራ እርምጃ በአስቸኳይ እንዲያቆም እየጠየቅን፤የፌዴራል መንግስት የዜጎችን ሰብአዊ መብት የማስጠበቅ ግዴታውን እንዲወጣ፤ የፈረመውን ዓለማቀፍ ስምምነትም እንዲያከብር እንጠይቃለን።
ሌሎች የሚመለከታቸው የሰብአዊ መብትና የዲፕሎማሲ ማኅበረሰብም ድርጊቱን እንዲያወግዙና መሰል አማራ ጠል የትግራይ ክልል አካሄዶች እንዲቆሙ ግፊት በማድረግ እንዲተባበሩን እንጠይቃለን።

**አማራ በልጆቹ ትግል ታሪኩን ያድሳል!**